

# የግንዛቤ ማስጨበጫ

## አይ ፒ ኤም ኤስ /IPMS/ ኘሮጀክት የኤች አይ ቪ ኤድስን ግንዛቤ በተመረጡ ወረዳዎች ሕብረተሰብ ውስጥ ለማስረጽ የሚያከናውነው ተግባራት

### በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያሉ እውነታዎች

- ወደ 1.3 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በበሽታው ተጠቅተዋል
- በየቀኑ 350 ሰዎች በበሽታው በመያዝ ላይ ናቸው
- ይህንኑ ያህል ሰዎች በኤች አይ ቪ ተዛማጅ በሽታዎች በየእለቱ ይሞታሉ
- እድሜያቸው ከ15-49 ከሚደርሱ ሚቾች መካከል 35 % ያህሉ የሞታ ቸው ምክንያት በኤድስ ነው
- በ 2,000 አጋማሽ የእድሜ ማራዘሚያ መድኃኒት ማግኘት ከሚገባቸው ወደ 280,000 ከሚጠጉ ተጠቂዎች መካከል መድኃኒቱን ያገኙት 35,000 ህሙማን ብቻ ናቸው
- የሴቶች ለበሽታው የመጋለጥ አጋጣሚዎች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ቢያንስ ከ1.2 በላይ መሆኑ ታውቋል

### የኤች አይ ቪ ኤድስን ግንዛቤ በሕብረተሰቡ ውስጥ የማስረጽ ተግባር በአይ ፒ ኤም ኤስ ኘሮጀክት ውስጥ በዋናነት የተካተተባቸው ምክንያቶች

- የገጠሩ ነዋሪ በኤች አይ ቪ /ኤድስ/ ወረርሽኝ ለማስተማር የግብርናው መስክ የሚያበረክተው ልዩ ሚና ስላለው
- ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በእርሻ ሥራ የሚሰማሩ ሰዎች ሕሙማንን ወደ መንከባከቡ እንዲያዘነብሉና በሞት ጊዜም የሚች ቤተሰቦችን በማጽናናት የሥራ ጊዜያቸው እንዲባክን ስለሚያደርግ በምርታማነት ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድር
- በአንድ ቤተሰብ ጥላ ሥር ከተሰበሰቡት አባላት የአዋቂዎች በሞት መነጠቅ በርካታ ጉዳቶችን ያስከትላል ይህም ለቤተሰብ አምራች የሆነ ጉልበት እውቀት ልምድ ያለውና የሥራ ጥበብን የተካነ ረዳትን ያሳጣል
- በሽታው የገጠር ነዋሪውን ማህበራዊ አደረጃጀ ሕብር ይዘትና የአርሶ አደሩን ቤተሰብ ግንባር ቀደም ፍላጎት እንዲቀየር ከማድረጉ ባሻገር አብዛኞቹ ገበያ ቀመስ የሆኑ የኤክስቴንሽን መልእክቶችን መና ያደርጋል

- የአይ ፒ ኤም ኤስ ፕሮጀክት በሸፈናቸው በክልሉ የገጠር ቀበሌዎች ያለው የኤች አይ ቪ የስርጭት መጠን ከ2% አንስቶ እስከ 5% ከመቶ በላይ ነው

- በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ ያለውን የኤች አይ ቪ ስርጭት ደረጃ ማወቅ አይ ፒ ኤም ኤስ በግብርናው መስክ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ በተጓዳኝ አርሶ አደሩን ስለበሽታው ሊኖረው የሚገባውን እውቀት በማስጨበጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይረዳል

- ከዚህም በተጨማሪ የአይ ፒ ኤም ኤስ ፕሮጀክት ኤድስን በማስፋፋት ወይም የኤድስ ተጠቂነትን በማዛመት ደረጃ ሚና እንደሌለው ማወቅ እና ይህንንም ማረጋገጥ እንዳለበት ያውቃል

## አይ ፒ ኤም ኤስ በተመረጡ ወረ ዳዎች በሚያከናውናቸው ተግባራቱ ውስጥ የኤች አይ ቪ ግንዘቤን የማስ ረጽ ሥራ የማካተት አላማዎች

- ኤች አይ ቪ በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ ያለውን ገጽታ ለማወቅ

- በተመረጡ ወረዳዎች ኤች አይ ቪ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽእኖ ለይተው ለማወቅ እንዲችሉ ለመርዳት

- በኤች አይ ቪ የመጠቃት አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶችን ከገጠሩ ኅብረተሰብ ከባለሙያዎች ጋር ሆኖ ሊያውቅ የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸትና ይህንንም በይበልጥ ሊሰሩ ከሚችሉ የሙያ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና በፕሮጀክት የተግባር መዘርዝሮች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ

- በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ሁሉ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያላቸውን እውቀት ማጐልበት

## የግንዛቤ ማስጨበጫና የኤች አይ ቪ መከታተያ ሰነድ አጠቃቀም

- ይህ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በርካታ በኤች አይ ቪ ዙሪያ ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራትን ዝርዝር ያካተተ በመሆኑ ስልጠናና የመስክ ውይይትን የመሳሰሉ የአይ ፒ ኤም ኤስ የስራ እንቅስቃሴዎች ሲታሰቡ ሰነዱን ማጤን ተገቢ ይሆናል

- ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያለውን ግንዛቤ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽና ስለ በሽታው ያሉ የግንዛቤ ክፍተቶችን አጉልቶ ለማሳየት የሚረዱ ተግባራት ሲታቀዱ የመከታተያ ሰነዱን በአግባብ አጠናቆ መሙላት ተገቢ ነው

## 1. ዓላማ፡- ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያለ ውን ግንዛቤ ማዳበር

### ተግባራት፡-

- የግንዛቤ ማኅበራትን የኅብረት ሥራ እና በንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ክፍሎችን የባህሪ ለውጥ የማሳያ ምሳሌ አድርጎ መጠቀም

- ከንግድና ከእርሻ ምርት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነገር ግን ብዙ ጊዜ በባህሪያቸው የግብርና ምርቶችን ከንግድ ሥራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሥራ ዘርፎችና ግለሰቦች ላይ ትኩረት መስጠት ለምሳሌ ነጋዴዎች ባለመደብሮች የመጓጓዣ ሠራተኞች ደላሎችና አነስተኛ ነጋዴዎች

- ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለማስተማር የገበያ ቀናትን በአጋጣሚነት መጠቀም

- ለኤች አይ ቪ የመጋለጫ ወቅት ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ ወቅቶች ለምሳሌ በመኸር እና በበአላት ከፍተኛ የማስተማር ሥራ መሥራት
- ስለበሽታው የገጠሩን ኀብረተሰብ ማስተማር የሚረዱ ተጨማሪ መንገዶችን ማፈላለግ:: ለምሳሌ አገር በቀል የሲኒማ ሥራዎችን እንዲመለከቱ ማድረግ
- ስለ ኤች አይ ቪ /ኤድስ የሚያወሱ ርእሶችን በመላው የአይ ፒ ኤም ኤስ የስልጠና ኮርሶች አውደ ጥናቶች የመስክ ጉብኝቶች ወዘተ ውስጥ እንዲከተቱ ማድረግ
- በየወረዳው የሚሰጡ የአሰልጣኞች ስልጠና ውስጥ የግብር የልማት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻዎች ተካተው ብቁ አሰልጣኞች ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ መፍጠር
- በቂ እና በደረጃ የተዘጋጀ ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ማስተማሪያና ማሳወቂያ የሚሆኑ የፁሑፍ መረጃዎች ለአካባቢው በሚሆን ቋንቋ ተዘጋጅተው በወረዳዎች በሚገኙ የክህሎት ማበልጸጊያ ጣቢያዎችና ለግብና ማስልጠኛ ተቋማት እንዲዳረሱ ማድረግ
- ማከፋፈያ ጣቢያዎች በቅልጥፍና እንዲሰሩ እና አላስፈላጊ መዘግየት እንዲወገድ ማድረግ
- አርሶ አደሮችን እና/ ወይም በእርሻ ስራዎች ወቅትን ጠብቀው የሚሰማሩ ሠራተኞችን ስለ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ሕይወታቸው ራእይ እንዲኖራቸው መርዳት
- ሴቶች ገቢያቸው እንዲዳብርና ተሰሚነት እንዲኖራቸው ማገዝ
- የግብይቱ ሥርዓት ይበልጥ ሴቶች የሚሳተፉበትና ቀና እንዲሆን ማድረግ
- የገጠሩን አካባቢ ለኑሮ ምቹ በማድረግ የነዋሪውን በተለይ የወጣቶች ፍልሰት መቆጣጠር
- ከአቅም ግንባታ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ የኤች አይ ቪ ስጋቶችን ለመቀነስ መጣር ለምሳሌ ስልጠናዎችን ሰልጣኞች ከሚኖርባቸው አካባቢዎች ርቀው እንዲከናወኑ አለማድረግ፣ ቢቻል ባል እና ሚስት አብረው ስልጠና ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት እንዲሁም ሰልጣኞች ከቤታቸው ወጥተው እንዲያድሩ የሚያስገድዱ ስልጠናዎችን መቀነስ

## 2. ዓላማ:- ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ የመጋለጥ አደጋን መቀነስ

### ተግባራት:-

- አርሶ አደሩ የግብአቶችን በቅርበት ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ በማመቻቸት ከቤቱና ከቤተሰቡ ርቆ እንዲጓዝ የሚያስገድዱ አጋጣሚዎችን መቀነስ:: ለምሳሌ ስለ ገበያ መረጃ የሚያገኝበትን ማእከል መፍጠር የጅምላ ግዢና ሽያጭ እንዲሁም ውል መዋወያ ስርአቶችን ማመቻቸት

## 3. ዓላማ:- በኤድስ ምክንያት ለሚከሰቱ ተጠቂነት ለአደጋዎች መጋለጥን መቀነስ

### ተግባራት:-

- በኤድስ በተጠቁ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ውስጥ የማስተዋወቅ ሥራ የሚሠራባቸው ተፈላጊ የሸቀጥ ምርቶችን በተከታታይነት ለማቅረብ የሚያስችል አምራች ኃይል መኖሩን ማረጋገጥ



- አዲስ የሚቋቋሙ ስራ ፈጣሪ ተቋማት ቀጣይነት ያላቸውና ቢያንስ ባለው አነስተኛ የምርት ግብዓት ላይ በዘላቂነት የሚቆይ መሆኑን ማረጋገጥ
- ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ዘላቂ የገቢ ማስገኛ ሊሆኑ የሚችሉ የገቢ ምንጮችን ማፈላለግ
- በኤድስ ተጠቂ ቤተሰቦች ላይ በማምረትናበግብይትወቅትየሚደርሱ ችግሮችን እንዲወጡ መርዳት
- ለምሳሌየሚያስፈልጋቸውንየጉልበት ድጋፍ መስጠት ምርቶቻቸውን ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያግዙ ቡድኖችን ማቋቋም፣ በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ተጠቂ ነጋዴዎችን ማደራጀት
- በበሽታው ተጠቂ ለሆኑ ቤተሰቦች አመቺ የሆኑ ገበያ እና የግብይት ሥርዓት እንዲኖር መርዳት ይህም ያላቸውን የሰብል ምርትም ሆነ የቤት እንስሳት በቀላሉ እንዲገበያዩ ከማድረጉም ሌላ ታማሚ የቤተሰብ አባላቶቻቸውን በቅርበት ለመንከባከብ እድል ይሰጣል
- የገበሬ ማኅበራትን ለተጐጂ አባላቶቻቸው የድጋፍ መስጠትና መንከባከብ ስራን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌወላጆቻቸውንበሞትለተነጠቁ ሕፃናት ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ
- ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርጉና የተመጣጠነ የገንቢ ምግብ ይዘት ያላቸው የሰብልና የእንስሳት ዝርያዎችን ማስተዋወቅ
- ሰፊ ቤተሰብ ባላቸው አርሶ አደሮችና የጉልበት ሠራተኞች ዘንድ መሠረታዊ ክህሎትን ማስፋፋት
- የሰብል ምርት ተዋራሾች በገበያ ማሰልጠንና ማስፋፋት ተግባር እንዲሳተፉ ማድረግ
- አነስተኛ የብድር ተቋማት የአጭር ጊዜ ብድሮችን ያለ ዋስትና ለተገልጋዮች ሊሰጡ የሚችሉበትን መንገድ

## 4. ዓላማ፡- አዳዲስ ግንኙነቶችንና የሥራ አጋርነትን መፍጠር

### ተግባራት፡-

- አዳዲስ የሥራ አጋሮች በአይ ፒ ኤም ኤስ የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ መፍቀድ፡፡ ለምሳሌ የኤች አይ ቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ ቤት በአውደ ጥናቶችና በስልጠናዎች ይሳተፋሉ
- በሥራ አጋሮች በጋራ የሚነደፉ የሥራ እቅዶችን ማመቻቸት /ለምሳሌ/ በሴቶች ጉዳይ እና በኤች አይ ቪ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ ቤቶች መካከል የማደረጉትን አይነት
- የሥራ አጋሮች ያላቸውን ቁሳቁሶችና ንብረት በጋራ የመጠቀም ልምድ እንዲዳብሩ ማበረታታት